ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በመስከረም 25 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ሥጋ የሰረቀ ፤ በመረቅ ይያዛል !

**ኢትዮጵያ፡-** ሀበሳዋ ብዙ ፤ ችግሯ ውጥንቅጥ፤ ታሪኳ ውስብስብ፤ ዜጎቿ ቅይጥ-ጉራማሌ ፤ ምሥጢሯ ጥልቅ፤ መልከዐ ምድሯ ዥንጉርሩና ወጣ-ገባ ፤ መሆኗንና የነዋሪዎቿንም ሥነአዕምሮና መስተጋብር በሚገባ ሳያውቁ፤ ሳይረዱ ፤ሳያጤኑ ፤ ሳይማሩ ሳይመረምሩ፤ እንዲያው በችኮላ፤ በሀገርና በሕዝብ ጉዳይ ዘው ብሎ መግባት፤ ከማይወጡበት ማጥ ውስጥ ግብቶ ራስን ማጥፋት ይሆናል። ኢትዮጵያ አትንኩይ ባይ ሀገር ነች። ዜጎቿም ለነፃነታቸው ቀናዒ ናቸው። ይኸንን ሃቅ ማወቅ አስፈላጊም ግዴታም ነው።

የእስካሁኖቹ መሪዎቿም ፤ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በሚገባ ሳያውቁ፤ ከሥልጣን ላይ የፈናጠጡና ፤ ብቸኛ የሀገሪቱ ችግር ፈጣሪዎች ሆነው ቆይተዋል። እስካሁንም ድረስ፤ በስዩመ እግዚአብሔር ፤ በሶሻሊዝምና ብሄር ነፃ አውጭ ስም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በደሎች ፈፅመዋል። እስካሁኑ ድረስ ግፉና በደሉ እንደቀጠለ ነው። በማንና መቸ እንደሚቆም መተንበይ አልተቻለም። እንዲያውም፤ ለሌላ አራተኛ ዙር መከራና ስቃይ በሀገሪቱ ላይ እያንዣበበ እንደሆነ ስጋታቸውን የሚገልፁ በርካታ የፖለቲካ ታዛቢዎች አሉ።

በመሪዎች ጥፋት፤ ሀገርንና ሕዝብን መበደል፤ ምን ያኽል ችግር እንዳመጣብን ፤ የቅርብ ታሪካችን ኸያው ምሥክር ነው ። ኢትዮጵያ፤ በቅርብ ታሪኳ፤ ለተተኪው ትውልድና ለራሷም መፃዒ ዕድል የሚያስቡላት መሪዎች አላጋጠሟትም።

ሥጋ የሰረቀ፤ በመረቅ እንደሚያዝ ሁሉ፤ ቃል -ኪዳን ያፈረሰም በክህደት መወንጀሉ አይቀርም። ለሥጋ ሌባ መያዝ ፤ መረቅ ሰበብ እንደሚሆን ሁሉ፤ በድንቁርና ላይ የተመሰረተ ድፍረትም፤ ለማነኛው ጥፋት ሁሉ ሰበብ ከመሆን አያመልጥም። ድፍረትን በትኅትና፤ አለማወቅን በትምህርትና በዕውቀት ካልያዙት፤ መጨረሻው ሀገር አጥፍቶ መጥፋት ይሆናል ። ለዚህ ክስተት እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው ፤ የደርግ መጀመሪያና መጨረሻ ታሪክ ነው ። የወደፊቶቹ የኢትዮጵያ መሪዎች ፤ " **ደርግን ያየኽ ፤ተቀጣ !** " ማለት አለባቸው። ከታሪክ መማር፤ ታላቅ ብልኅነት መሆኑን ሁሉም ሊያውቀው ይገባል !

ያለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚያስረዳው፤ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ማንነት እንደማያውቁት ሁሉ፤ ሕዝቡም የነርሱን ዕውነተኛ ማንነት ያውቀዋል ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻል አለመሆኑ፤ እየዋለ እየታደረ ግልጽ እየሆነ መጥቷል ብለው የሚያምኑ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ። በዚህ ምክንያት፤ ሳይተዋወቁ አብሮ ለመኖር የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ፤ ሆድና -ጀርባ ከመሆን ያለፈ ትርጉም የሌለው ሆኖ ቀርቷል። ሆድና -ጀርባ ሆኖ ለመኖር ስለሚጥሩ፤ ሕዝቡና ወያኔዎቹ ፤ በጥርጣሬ እየተያዩ ወንዙን ለመሻገር ይሞክራሉ። የማይተማመኑም በመሆናቸው፤ በየወንዙ ይማማላሉ። " **የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል ።** " እንዲሉ !

የዚኽ ሁሉ ችግር መንስዔው፤ ወያኔዎቹ፤ የነበረችውን ኢትዮጵያን አፍርሰን ፤ ያልነበረች ሌላ ሀገር እንደገና መስራት አለብን የሚል ቅዥት ማስተናገዳቸው ነው። ሀገር መገንባት ፤ ሀገር እንደማፍረስ ቀላል እንዳልሆነ ግን አልተረዱትም።

**" እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ፤ በግለሰብ ደረጃ፤ ብርቱና ጀግና፤ አይበገሬና አትንኩኝ ባይ መሆኑ ባይካድም፤ በአንድነት ግን አብሮ ተስማምቶ ኅብረት መፍጠር ስለማይሆንለት፤ እኛን አያሰጋንም** "ብለው በማመን ፤ወያኔዎች ፤ተደላድለው እስካሁን በሥልጣን ለመቆየት በቅተዋል። ወያኔዎቹ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ ለመስረቅ ባይችሉም እንኳን ፤ የሀገራችንን ባዕዳን ጠላቶችን ልብ ለመስረቅ የሚያስችል ክኅሎት ግን አግኝተዋል ። በዚኽ ምክንያት ፤ የባዕዳኑን ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ለማግኘት በቅተዋል።

በወያኔ ስር የተሰባሰቡት ግለሰቦች፤ ከአክራሪው አልባንያ ሶሻሊዝም ዕምነታቸው ተስፈንጥረው፤ በአንድ ቀን ዥምበር ለምዕራቡ ካፒታሊዝም ሲሰግዱ፤ ትንሽም ቢሆን አልተሸማቀቁም። መርሕና ወያኔ ወትሮም ቢሆን ስለማይተዋወቁ፤ ይኽ ባኅርያቸው ማንንም አያስገርም ። ይኽ ባኅርያቸውን ግን ከባኅል የወረሱት ይመስላል። በትግርኛ አንድ ተረት አለ። ይኸውም " ዝበረቐ ፀሃይና ፤ ዝነገሠ ንጉስና " ይባላል። ትርጉሙም "የፈነጠቀው ፀሃያችን፤ የነገሠው ንጉሣችን " እንደ ማለት ነው ። የወያኔዎቹን ሥነልብና በሚገባ የላወቀ ተቃዋሚ ኃይል ፤ በተጨባጭ የሚዋጋውን ሥርዓት አራማጆች ጠባይ፤ ባግባቡ ካላወቀ ፤ ድልን ለመቀዳጅት የሚያስችለውን ዕድል አያገኝም። የሚዋጉትን ጠላት በሚገባ ማወቅ፤ ጠላትን ለመደምሰስ ያስችላል።

" ወያኔ የትም አትደርስም " ሲሉ የነበሩ ተላላዎች ግን ይኽንን ሃቅ ማመን አይፈልጉም። የሕዝብን ልብ መማረክ ያልቻለ፤ መንግሥትም ይሁን ተቃዋሚ ኃይል፤ ስንዝር መንገድ ወደፊት መራመድ አይችልም ። አሮጌን ፍይልና የተረሳን ዶሴ እያገላበጡ መኖር፤ " **ትዝ አለኝ የጥንቱ !** " የሚል ዜማ ከማሰማት ያለፈ ፋይዳ አያስገኝም ። በዚህ ምክንያት ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ፤ የሀገራችን ጉዳይ፤ **ባለህበት - ዕርግጥ** ሆኖ ቀርቷል። የሕዝቡ ትግል " እየፈጩ ጥሬ " በሆነ ደረጃ ቆሞ የቀረውም፤ በዚኽ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል ። እስካሁን ድረስ " ከባለህበት ዕርገጥ " ዳንኪራ ሰብሮ በመውጣት (Break through ) ዕመርታ ማሳየት አልታቻለም።

ባለፈ ታሪክ መዝናናትና፤ በአሮጌ በሬ ማርስ፤ ልክ የደረቀ ወንዝ እንደ መሻገር፤ ይቆጠራል እንጅ፤ የተመኙትን ውጤት አያስመዘግብ። አያስመስግንምም ። አንድ ሕዝብ ፤ አኩሪ ታሪኩንና ጀግንነቱን እንደ መዝናኛ እየተጠቀመ የሚረካ ከሆነ ፤ አዲስ ታሪክ ለመስራት የሚኖረው ፍላጎት፤ ቁጭትና ጉጉት ጫጭቶ ይቀራል ። አሻግሮ ለማየት የሚያስችለውንም ራዕይ የሚያይበት ተስፋ ሁሉ ይጨልምበታል ። አዲስ ዐመት በመጣ ቁጥር፤ ለበዐል ማክበሪያ የሚሆነውን የተለምዶ ዝማሬና መወድስ-ቅኔ ማሰማት ብቻውን ተተኪውን ትውልድ አያረካውም። አዳዲስና አቅጣጫ ሰጭ የሚሆኑ ተጽዕኖ ፈጣሪ ዐውደ- ኃሳቦች እስካለመጡ ድረስ፤ የጋለ ተስፋ የሚኖረውን ትውልድ መፈጠር አይቻልም።

ጀግኖችንና ሠማዕታት ዜጎችን ማክበርና መወደስ ተገቢም አስፈለጊም መሆኑ ባያከራክርም፤ በተለይ ግን ፤ለሀገር ባለውለታዎች የሚገባቸውን ዎሮታ መንፈግ፤ " **አየ አንቺ ሀገር፤ በዕውነት ሰው ይውጣብሽ !** " የሚል ርግማን ሊያስከትል ይችላል። እስካሁንም የሆነው ፤ በአመዛኙ ይኸው ነበር ። የኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግር እጅግ ያሳሰባቸው ፤ አንድ ሀገር ወዳድ አዛውንት ፤ ቢጨንቃቸው የሚከተለውን ተናገሩ ይባላል ። እንጠቅሳለን ፤ " **የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለሀገራቸው ሲሉ የወደቁትን ጀግኖች ሠማዕታት ተዝካርና ሠደቃ ካላወጣ፤ ሌሎች አዳዲስ ጀግኖች ያወጣሉ ብየ አላስብ !** " ሲሉ ቁጭታቸውን እንደገለፁ ይነገራል ። " የጨነቀው ፤ ሙቅ አነቀው " እንደሚባለው፤ እኝኽ አዛውንት ጭንቀታቸውን ቢያካፍሉ አይፈረድባቸውም ።

የቅርብ ታሪካችን እንደመዘገበው፤ ከፋሽስት ጣሊያን ወራሪ ኃይል ጋር ሲፋለሙ የነበሩትን ዕርበኞች የስቅላት ፍርድ ከሰጠ በኋላ፤ ሬሳቸውን በአድባባይ ሰቅሎ አንድ ቀን ሙሉ አላፊ- አግዳሚው እንዲመለከተው ያደርገን ሥር ዓት አሳልፈናል ። ይኽ አልበቃ ብሎ፤ ተተኪው የደርግ አምባገነን አገዛዝ በተራው ፤ ህፃናትን እየገደለ፤ ሬሳቸውን በየጎዳናው ዘርግቶ የውሻ መጫዎቻ ከማድረጉም በላይ፤ የሟቾቹ ወላጆች የልጆቻቸውን አስከሬን ለመውሰድ ገንዘብ እንዲከፍሉ ተድርጓል። ደርግን የተኩት ወያኔዎችም፤ እንደ ደርግ የተቃዋሚዎቻቸውን ሬሳ ባይሸጡም ፤ ሀገርን በመሸጥ ግን ታሪክ አስመዝግበዋል ።

ይኸንን ሁሉ ለመጥቀስ የተፈለገው፤ በታሪክ ግንዛቤነቱ እየተስተዋለ፤ ለመጭው የሀገራችን ዕድልና ተስፋ መለበሚያ ሆኖ እንዲያገለግል በመመኘት ነው። ለነገው ብሩኅ ተስፋ፤ ዛሬ ካልተሰበበት፤ የሚጠበቀው ለውጥ በሚመጣበት ጊዜ ፤" ቃሪያ ለመቀንጥስ " ሩጫና መደናበር እንዳይከስት አስቀድሞ ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንደሚኖርብን ለማስገንዘብ ነው።

ትላንት -ከትላንት በስቲያ ፤ አንዳችም በቂ ዝግጅት ሳይደረግ በመቅረቱ፤ ሀገራችን በተደጋጋሚ መልካም ዕድሎቿንና አጋጣሚወቿን አጥታለች። ዛሬም ሆነ ወደፊት፤ ተመሳሳይ ፤ የአግኝቶ ማጣት አጋጣሚ እንዳይገጥማት ያሰጋል። የለመደ፤ የሥጋ ሌባ፤ በመረቅ ይያዝ፤አይያዝ ግድ የለውም። ልማደኛ ሌባ፤ሁሉ ጊዜ፤ " **ካላዩኝ አመልጣለሁ፤ ከዩኝ እስቃለሁ** " በሚል ሥነ ልቦና ፤ ሌብነቱን ስለሚፈጽም፤ ስርቆቱ ፤ ታወቀበት/ አልታወቀበት፤ ለእርሱ ለውጥ አያመጣበትም። " ሌባ ላመሉ ዳቦ ቢልስም " ሥጋ ሰርቆ፤ በመረቅ ተያዘ፤ አልተያዘ ፤ መስረቁን የቀጥልበታል እንጅ፤ አያቆመውም። ለመንግሥት ሥልጣን የሚያቋምጥም እንደዚሁ በጠነከረ ሕዝባዊ የፖለቲካ ትግል መቆጣጠር ካልተቻለ፤ የአምባገንን አገዛዝ መመስረቱን አይተውም ።

በመሠረቱ፤ " የሰው ልጅ ፤ ሰውን ካላመነ፤ ሌላ ማንን ሊያምን ይችላል ?" የሚለውን ኃሰብ፤ በጥያቄ ደረጃ ማስተናገድ ባይከብድም ፤ በፖለተካ መርኅ አኳያ ፤ ግን ሕዝብ ከሕዝብና ከሚመሰርተውም ሥር ዓተ- መንግሥት ጋር በዘለቄታ ሊተማመንበት የሚችለው በጋራ ተስማምቶ በሚመሰረተው በጋራ ተቋም (INSTITUTION ) ላይ ብቻ መሆን አለበት ፡፡ እስካሁን ድረስ የሕዝቡን ሙሉና -ነፃ ተሳትፎ፤ ይሁንታና ቁጥጥር የተጎናፀፈ ሕዝባዊ ተቋም የለንም ። እየመጣ የሚሄደው ሁሉ የየራሱን ድንኳን እየሰራ የሕዝብ መጨቆኛ መሳሪያ እያደረገ ከቆይ በኋላ፤ እርሱ ሲጠፋ ድንኳኑም አብሮ ይፈርሳል። የንጉሣዊንና የደርግን ተቋማት ይጤኗል ! የወያኔም ተቋማት፤ እስከ ግሳንግሳቸው ተመሳሳይ ዕድል እንደሚገጥማቸው ምንም ጥርጥር የለም። ዕድሜ የሚኖረው፤ የማየት ዕድል ይኖረዋል ። እስከዚያው ድረስ ግን ፤ ልብ ያለው ልብ ይበል! ልብ የሌለው ደግሞ ልብ ገዝቶ ሀገሩን ከጥፋት ለማድን በሚደረገው ትግል፤ የራሱንን ድርሻ ይውጣ !

ፈራሾቹ ተቋማት ፈርሰው ፤አዲስ ተቋማት መተካት የግድ ነው። ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ያገኙ ነፃ ተቋማትን ለመመስረት ግን፤ ከአሁኑ መዘጋጀት ያስፈልጋል ። እስካሁን ዝግጅቱ መድረጉ ቀርቶ፤ እንዲያውም በኃሳብ ደረጃ ቢሆን የተሰበበት አይመስለም። በየትኛውም አካባቢ ዝግጅት ለመኖሩ ፍንጭ አይታይም። ከእንግዲህ ወዲያ አዲስ ለውጥ ሲከሰት፤ ሀገሪቱን እንደ ቤተ- ሙከራ (EXPERIMENT ) መጠቀሙ መቅረት አለበት። ያ በደልና ጥፋት አልቋል መባል አለበት።

ዝግጅት ያስፈልጋል ስንል፤ የሚከተሉትን ጠቃሚ ጉዳዮች በማሰብ ነው፡-

**1ኛ.** በሄራዊ የጋራ ሠነድ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ አልተዘጋጀም እያልን ነው።

**2ኛ.** የጋራ ሀገር መኖር አለባት የሚለውን ጥሪ፤ የተቃዋሚ ጎራ አሁንም ጆሮ ድባ ልበስ ብሎ ተቀምጧል ማለታችን ነው።

**3ኛ.** የኛን ችግር፤ በዕዳን ይፍቱልን ብለን እንርሱን ደጅ- መጥናቱን አቁመን፤ የራስችንን ዕድል ወሳኞቹ እኛው ራሳችን እንሁን እያለን ነው ።

**4ኛ.** እረ ፤ ለመሆኑ፤ ሀገራችን የደረሰችበትን የጥፋት ጠርዝ ከልባችን የተረዳነው **ስንቶቻችን ነን ?** የሚል ጥያቄ እያነሳን ነው ።

**5ኛ.** የአራቱን ጥያቄዎች መልሶች አንድ ላይ በመተባበር ጠይቀን ፤መልሱን በጋራ አግኝተን፤ ሀገራችንን ከጥፋት አናድናት ብለን ጥሪ እናቀርባለን ።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !**